ፍኖተ ዴሞክራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ
Finote Democracy Voice of Ethiopian Unity
Efdpu@aol.com www.Finote.org
ፕሮግራም፣ ረቡዕ እሁድ ከምሽቱ ሁለት ሰአት እስከ ሶስት ሰአት በ 25 ሜትር ባንድ
Programm. Wednesday and Sunday 8.00 PM — 9.00PM on 25 meter band

***የፍኖተ ዴሞከራሲ የኢትዮጵያ አንድነት ድምጽ ሀተታ***
***ቀን ሚያዚያ 20 ቀን 2007 ዓ.ም. የተላለፈ***

## ከመፍሰስ የማይደርቀው

## የኢትዮጵያ ደም !

" እንደ ፍልስጤም ደም በሲናይ በረሃ ሁሌ እንደሚፈሰው፤ "

ይባል ነበር ዱሮ፤

የኢትዮጵያም ንፁህ ደም፤ በሊቢያ በረሃ ፈሰሰ ዘንድሮ !

ለአለፉት አምሳ ዓመታት፤ የኢትዮጵያውያን ደም፤ ምድሪቷን እንደ ጎርፍ ሲያጥለቀልቅ ቆይቷል።እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ፤ ይህ የንፁሃን ደም፤ ሲጎርፍ የነበረው በሀገራችን ውስጥ ተከልሎ ነበር። ይህ ደም በአሁኑ ወቅት፤ ልክ እንደ ዐባይ ወንዝ፤ ድምበር በመዝለል እየጎረፈ፤ የሌሎችኑ ሀገራት መሬት እያጥለቀለቀው ይገኛል ።

ዛሬ፤ በስደት ተበታትነው የሚገኙት ኢትዮጵያውያን ወገኖቻችን፤ በጭካኔ ሁኔታ ዘግናኝ ግድያ፤ በየቦታው እየተፈፀመባቸው ይገኛሉ። ንፁህ ደማቸውም በረሃውን እያጥለቀለቀው ይጎርፋል ። የሀገራችን ዜጎች፤ የአንድ ኢትዮጵያ ልጆች፤ እንደ ጭዳ ከብት በየቦታ እየታረዱ ናቸው። አረመኒያዊ ተግባር በተሞላበት የጭካኔ አገዳደል ተረሽነዋል። በስለት ተቆራርጠዋል። ዐይናቸው ተሸፍኖ አንገታቸውን ቆርጠዋቸዋል። በዚህ ውጭ ነፍስ ውጭ ግቢ የመከራ ወቅት ግን ሊያድናቸው የደረሰ አልተገኘም ። የሎሄ! የሎሄ እያሉ መራራን የሞት ፅዋ ጨልጠዋል። የአባት የናታቸውን የጀግንነት መሥዋዕት ተቀብለው ወደ ማይቀረው ዓለም ሄደዋል። የኢትዮጵያዊነትን ማነነትና ክብር እየጠበቁ፤ ሃይማኖታቸውንና ዕምነታቸውን አስከብረው እንደ ጭዳ ከብት ታርደዋል ። ክርስቲያን ወገኖቹን፤አሳልፎ አልሰጥም በማለት፤ የተከራከረው፤ የእስልምና ዕምነት ተከታይ ዜጋችን፤ የጓደኞቹን ፅዋ እንዲቀበል ተደርጓል ። ለሃይማኖታቸው ቀናዒ የሆኑ ወገኖቻችንም፤ ሃይማኖታችንን አንለውጥም በማለታቸው፤ እንደ መሥዋዕት ጠቦት ተሰውተዋል! በሃይማኖት የሚያምን ዜጋ ሁሉ፤ በዕምነቱ ፀንቶ ኮርቶ እንዲኖር፤ ተምሰሌት ሆነው አልፈዋል ።

እንደ አንደ አብረሃም፤ ልጅ እንደ ያዕቆብ ከመሰዋት ሊያድናቸው የመጣ መለኮት ግን አልነበረም ። ንፁህ ደማቸው ግን በምደረበዳ ይጮኻል! ይማልላል! ሰሚ እስኪያገኝ ድረስ፤ ጩኸቱን ይቀጥላል ! ምናልባት የእነርሱ የሎሄ ጩከታቸው የሀገራቸውን የኢትዮጵያን ነፃነት ያበስር ይሆናል !

በደቡብ አፍሪካ፤ በመካከለኛው ምሥራቅ፤ በሲናይና በሊቢያ በረሃዎች፤ በሜዲተራኒያን ባህር፤ በቀይ ባህር፤ በቤይሩት፤ በካታርና በአቡዳቢ ከተሞች ሁሉ የወገኖቻችን ንጹህ ደም በግፍ ሲፈስስ መላው የዓለም ሕዝብ ሰምቷል ። ተመልክቷል ።

በሲናይ በረሃ ውስጥ ሳይሞቱ በህይወታቸው እያሉ፤ ኩላሊታቸውን አውጥተው፤ ልክ እንደ መኪና መለዋወጫ ዕቃ ወንጀለኞቹ፤ ሸጠውታል ። በ21ኛው ክፍለ-ዘመን ይህ ዓይነቱ ኢሰብዓዊና ዝግናኝ ደርጊት ይፈፀማል ብሎ ማመን ቢያስቸግርም፤ ይህ ዘግናኝ ድርጊት ግን በወገኖቻችን ላይ ተፈፅሟል። ወንጀሉም ተመዝግቧል ።

በስደት ላይ ያሉ ወገኖቻችን፤ እንደ በግ ታረዱም፤ ተረሸኑም፤ በዕሳት ተቃጠሉም፤ በህይወት እያሉ፤ ኩላሊታቸው ተቆርጦ ለገበያ ተሸጠም፤ በባህር ሰጠሙም፤ በየምድረበዳው ቀልጠው ቀሩም፤ እነርሱን የሚያድን ግን አስካሁን አልተገኘም። ደም መላሽ አልደረሰላቸውም ።

ሁሉም በየቤቱ የደም ዕምባ ያለቅሳል። በየዳሱ ሀዘን ተቀምጧል። ኢትዮጵያም ከል ለብሳለች። ሀዘንተኛው ሕዝባችንም ከማልቀስ ያለፈ ርምጃ ሊወስድ አልተቻለውም። የሚሰራው ቅጥ-አምባሩ ጠፍቶበታል። መሪ አጥቶ ይዋልላል። የሀገራችን ሁኔታ እስካልተለወጠ ደረስ ይህ ብሄራዊ ሀዘን ይቀጥላል። የችግራችን ምንጭ አስካልደረቀ ድረስም፤ በከፋ-በከረፋ መልኩ መቀጠሉን ይቀጥላል።

ኢትዮጵያ የራሷ የሆነ ኢትዮጵያዊ መንግሥት አስካላገኘች ድረስም ሁኔታው በአሳዛኝ መልኩ ይቀጥላል። ዘፀአቱ- ስደቱ፤ ግድያው ዕልቂቱ፤ መከራው ችግሩ፤ ውርደቱ ጥቃቱ፤ ችንፈቱ ቁጭቱ ሁሉ እየተነባበረ ይፈራረቃል። የኢዮጵያውያን ንፁህ ደምም፤ በየቦታው ይጎርፋል። የዓለምን ምድር እስከሚያረሰው ድረስ ይጥለቀለቃል ። ያጥለቀልቃል!

የዓለም ሕዝብ፤ ርኅራሄውን አልነፈገንም። ከቀጣዩ መከራችን ግን ሊያድነን አልተቻለውም ። እኛም ያድነናል ብለን አናስብም። አንጠብቅምም። በዓለም ዙሪያ የሚገኙ ደጋግና ርኅሩኅ ሰዎች ሁሉ፤ የሃዘን ዕምባቸውን አፍስሠውልናል ።

በ1966ዎቹ ዓመታት በደረሰብን ታላቅ የርሃብ መቅሰፍት፤ ሰላም ወዳዱ የሆኑ የመላው ዓለም ሕዝብ፤ የርሃባችን ማስታገሻ የሚሆን የአስቸኳይ እርዳታ ችሮናል ። አልቅሶልናል ። “ ዓለም እኛ ነን !“ ( We Are Th World ! ) ብሎ ደርሶልናል፡፡ ዘምሮልናል። አልቅሶልናል። እኛም ቢሆን ዕምባ አልቸገረንም እንጅ፤ መላው ዓለም ባፈሰስልን ዕምባ ልባችን ተንከቷል። ውለታን ለመክፈል ባንታደልም፤ ለዓለም ሕዝብ ሁሉ ባለውለታችን መሆኑን እናውቃለን።

ዛሬም፤ ልክ እንደ ረሃቡ ጊዜ፤ በወገኖቻችን ላይ በደረሰው አስቃቂ ግድያ መላው ዓለም የሀዘናችን ተካፋይ እንደሆነ እንረዳለን። ሳይሆንልን እየቀረ ነው እንጅ፤ እኛ ኢትዮጵያውያን ባለውለታዎቻችንን አንረሳም ። እናከብራቸዋልን ። እናመስግናቸዋለንም ! ልክ እንደ ትላንቱ ፤ ዛሬም ዓለም ያለቅስልናል ። በዳግመኛ ሀዘናችን ተካፋይ ስለሆነም እንመስግናለን ። የሀዘናችን ተከፋይ በመሆኑ !

የኢትዮጵያውያን ደም፤ በሲናይ በረሃ፤ በሊቢያ በረሃ እንዲህ የሚፈስሰው፤

በደቡብ አፍሪካ፤ በአደን ሠላጤ ፤ ቤይሩት ከተማ የሚንቆረቆረው ፤

ያንን ምድረባዳ ወርዶ፤ አጥለቅልቆ ፤ በጎርፉ ሲያረጥበው ፤

ምን ኃይል ተገኘና ሄዶ የሚያቆመው ! ምንጩን የሚያደርቀው !

እያለ የሀዘን መልዕክቱን እያስተላለፈ ነው ።

ዓለም፤ በኢትዮጵያ ላይ የደረሰውን መከራ ተገንዝቦ የሀዘን ተከፋይነቱን ቢገልፅም ቅሉ፤ ኢትዮጵያውያን ዛሬ፤ ከጥቃት ሊያድናቸው የሚችል የራሳቸውና ራሳቸውም ያቆሙት መንግሥት አላገኙም ። የሀገሪቱን ክብር የሚያስከብር፤ ብሔራዊ ጥቅሟን የሚያስጠብቅ፤ የሌላት ሀገር ሆና ትገኛለች። የመከራውና የስቃዩ ምንጭ እስካልደረቀ ድረስ፤ ስደቱ፤ መከራው፤ ጥቃቱ፤ ግድያውና እልቂቱ በከፋ መልኩ ይቀጥላል።

የሀገሪቱን መከራ ለማስቆም፤ በግድ፤ የዚህ ሁሉ ዓይነተኛ ተጠያቂ የሆነውን ወንጀለኛ አገዛዝ ማስወገድ አስፍላጊ ብቻ ሳይሆን፤ አንገብጋቢም ነው።

የዛሬዋ ኢትዮጵያ የመከራውን ሁሉ መዓት ያመጣው ወያኔ ነው። እነኝህ ወጣት ኢትዮጵያውያን፤ ሳይወዱ በግድ ከሀገራቸው እንዲሰደዱ ያደረጋቸው፤ በዘር ተደራጅቶና ታጥቆ፤ ራሱን የትግራይ ነፃ አውጭ ድርጅት ነኝ ብሎ የሚጠራውና ሥልጣን የጨበጠው ጎሰኛና ፋሽስታዊ ድርጅት ነው። ወገኖቻችንን በአረመኔ እጅ እንዲወድቁ ምክንያት የሆነው ይህ መሰሪ የብሄር ድርጅት ነው። በገዳይ አስገዳይ ወንጅል ተጠያቂው ራሱ ወያኔ ብቻ መሆኑ አይቀሬ ነው ። አሰድዶ፤ ለገዳይ አሳልፎ ሰጥቶ አሳርዷቸዋል ። አስገድሏቸዋል። የወንጀሉ አባሪ-ተባባሪ ነው ።

በሊቢያ የታረዱት ልጆቻችን፤ ወንድሞቻችን ተሰድደው ለዚህ አሰቃቂና ዝግናኝ ግድያ የተዳረጉት፤ ልክ " ያባቱን ውርስ ድርሻ ተቀብሎ እደኮበለለው አባካኙ ልጅ " በጥጋብና በትዕቢት ተገፋፍተው አይደለም። በሀገራቸው የሚበሉት የሚቀምሱት አጥተው የዕለት ጉርስ፤ የዓመት ጉርስ ለመፈለግ ሲሉ በመገደዳቸው ብቻ ነው። በትውልድ ሀገራቸው፤ የመኖራቸው ተስፋ ስለተሟጠጠባቸው ነው። ሰርቶ ለመብላት፤ በልቶ ለመሰንበት፤ ስንብቶ ለመኖር፤ ኑሮም የሕይወትን ጣዕም ለማግኘት ምኞታቸውና ተስፋቸው ስለመነመነ ብቻ ነው። ይኸም ሊሆን የቻለው፤ ወያኔ የዘረጋው ድንባራና-ሸውራራ የፖለቲካ ሥርዓትና ምስቅልቅሉ በወጣው የኢኮኖሚ ብወዛና ብዝበዛ ምክንያት ነው።

ለሕይወት አስፈላጊ የሆኑ እንደ ምግብ መጠጥ ያሉትን ማጣት ብቻ ሳይሆን፤ መሠረታዊ የሰው ልጅ መብቶችንም ማጣታቸው፤ ሳይወዱ በግድ እንዲሰደዱ ሆነው፤ እጅግ ዘግናኝ በሆነ አሰቃቂ ግድያ፤ በወጣት ዕድሚያቸው፤ ህይወታቸው እንዲያልፍ ተደርጓል ። ይህን አሰቃቂ ወንጀል ታሪክና ትውልድ ሲያወግዘው ይኖራል። ለኢትዮጵያ ሕዝብም የማይረሳ የመንፈስ ስብራት፤ የልብ ቁስልና የአዕምሮ ጉዳት አሳርፎበት አልፏል ።

የኢትዮጵያ ሕዝብ ፤ እየየ ! እየየ ! ከማለት ያለፈ ሊያፅናናው የሚችል መዳህኒት አላገኘም ። ሊወስደው የሚችለውንም ርምጃ ምን እንደሚሆን አልተረዳውም። ቢያውቀውም ርምጃ ለመውሰድ የሚችል አቅምና ኃይል ለጊዜው አላገኘም ። ሀገራዊ ራዕይ ኖሮት ሕዝቡን ሊያስተባብር የሚችል ሀገር አቀፍ ድርጅት እስካሁን ነጥሮ አልወጣም ።

ይህ ሁኔታ በበኩሉ፤ ሀገሪቱን ባለቤት የሌላት ምድር እንድትሆን አድርጓታል ። የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ደግሞ፤ ኢትዮጵያውያን በሀገራቸው ቀርቶ ተሰድደው በሚኖሩበት የባዕድ ሀገር እንኳን ሳይቀር፤ እንደ ከብት እንዲታረዱ አድርጓቸዋል። በሊቢያ በረሃ የተፈፀመባቸው አስቃቂ ግድያ የዚህ ሁሉ ድምር ውጤት ነው። ዛሬ የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ በሊቢያ የታረዱትን ልጆቹን ሀዘን ለመወጣት እንኳን አልቻለም። ወጥቼ ላልቅስ ቢልም፤ የወያኔ ነፍስ-ገዳይ ጦር በአደባባይ ደብድቦ በታትኖታል። ሀገራችን ዛሬ፤ ሀዘንን በአደባባይ ለመግለፅ እንኳን ነፃነት የማትሰጥ ምድር ሆና ትገኛለች።

" በዕንቅርት ላይ ጆሮ ደግፍ" እንዲሉ፤ ሀዘኑን ለመግለፅና ግድያውንም ለማውገዝ ሠላሚው ሰልፍ የወጣውን የአዲስ አበባን ሕዝብ፤ ግራጫ ለባሹ የወያኔ ነፍሰ ገዳይ ቡድን ፤ በቆመጥ እየፈነከተና እያቆሰለ ብዙ ጉዳት ካደረሰ በኋላ ፤ ሠላማዊ ሰልፉን በትኖታል። ይህንን ማድረጉ ያልተጠበቀ አልነበረም። የሕዝቡ ቁጣና ተቃውሞ ከቁጥጥር ውጭ በመሆን፤ ወደ ሕዝባዊ አመፅ ከተለወጠ፤ ድምጥማጡ እንደሚጠፋ ስለሚያውቀው፤ ሕዝባዊ ማዕበሉን አስቀድሞ መከላከል ነበረበትና ያንኑ ነው ያደረገው። አመጹን ለጊዜው ያስተላለፈው ጊዚያዊ ዕፎይታ ለማግኘት ካልሆነ በስተቀር፤ ሕዝባዊውን አመፅ ሊያዳፍነው አይችልም። አመፁ ተጠናክሮ መቀጠሉ አይቀርም ። የታሪክ ሀቅ ነውና !

አምባገነኖች ሁሉ፤ ነፍሰ ገዳይ ሠራዊቶቻቸውን፤ በልዩ ልዩ ቀለማት ያንጸባረቀ፤ የወታደር ዩኒፎርም እያለበሱ ወደ ግድያና ድብደባ እያሰማሩ፤ ዕድሜያቸውን ለመቀጠል ይጥራሉ። የኢጣሊያኑ ግራዚያኒ፤ ካሚሻ ኔራ/ ጥቁር ሸሚዝ ለባሽ ነፍሰ ገዳይ ፖሊሱን አስማርቶ አዲስ አበባ ላይ ብዙ ሽ ሕዝብ በጊዜው አስፈጅቷል። ደርግም በበኩሉ በጊዜው አረንጓዴ ለባሽ የነበልባል ጦር አስታጥቆ ብዙ ሕዝብ ጨርሶና አስጨርሶ ሄዷል። ወያኔም በተራው፤ ግራጫ ለባሽ ጦር አሰልፎ ግድያውን ቀጥሏል። የናዚ ጀርመንም እንደዚሁ፤ ቡናማ ሸሚዝ ለባሽ ( ብራውን ሽርት ) የጌስታፖ ገዳይ ሠራዊት እንደነበረው፤ በታሪክ ይታወቃል። ሁሉም አምባገነን ሥርዓቶች ጠፍተዋል። ወያኔም ተራውን ይጠብቃል ።

ሕዝባዊ ትግሉም፤ ሕዝባዊ አመፁን እያካሄደ ይቀጥላል ። በመጨረሻም በወያኔ ከርሰ-መቃብር ላይ፤ የኢትዮጵያን ትንሣዔ ያረግግጣል ። የኢትዮጵያ ሕዝብ፤ ለዕድሜህ ዕድሜ ይስጠው ! አንድነትህን ጠብቀህ፤ ኅብረትህን አጠንክረህ፤ ኀልውናህን እያስከበርክ፤ በአንድ ላይ ቆመህ ታግል። የማታ ማታ ድሉ ያንተ ነው። በጨቋኙ ጠላትህ ከርሰ-መቃብር ላይ ሀገራዊ ነፃነትህን ታስከብራለህ !

" እኔ ከሌለሁ ሀገሪቱ ትፈራርሳለች " እና " አሜሪካ እስከደገፈኝ ድረስ ከሥልጣኔ አልነቃነቅም " የሚላቸውን ከንቱ ማጭበርበሪያዎች፤ እንደተደጋጋሚ የፕሮፓጋንዳን ስልት እየተጠቀመ ፤ ወያኔ ራሱን ያታልላል። ሁለቱም ውሃ የማይቋጥሩ የፖለቲካ ቆማሮች ናቸው። ኢትዮጵያ ሀገራችን ከወያኔ በፊትም

ነበረች። አሁንም አለች። ወደፊትም ትኖራለች። እንዲያውም የወያኔዎቹ መወገድ ፤ የሕዝቧን አንድነትና ኅብረት በማጠናከር የሀገራችንን ነፃነትና ሉዓላዊነት ያረጋግጥልናል ።

ይህ እንዳለ ሆኖ ግን፤ በዕርግጥ፤ አሜሪካኖች ወያኔን ለሥልጣን አብቅተውታል። በመሳሪያነትም እየተጠቀሙ ታማኝ አሽከር አድርገውታል። የጥቅማቸው አስጠባቂ ስለሆነላቸውም፤ ሲጠሩት አቤት ሲልኩት ወዴት የሚል የቤት አገልጋይ ሆኖላቸዋል ። ይህ ግን ፤ እከክልኝ ልከክልህ ፤ ከሚል ከጊዜያዊ የጥቅም ለውውጥ ያለፈ ዘለቄታ አይኖረውም። በሀገሮች ዲፕሎማሲ የቆማር ጨዋታ ደግሞ ዘላቂ የሚባል ወዳጅነት ፈፅሞ አይኖርም ። በመሆኑም፤ የወያኔና የምዕራብያውያን ጥቅም እፍ ሲሉት ሽልጥ ነው። ራቅ ሲል፤ የኢራኑን/ ሻህ ንጉሠ ነገሥትና ቀረብ ሲል ደግሞ የግብፁን ፕሬዝደንት ሁስኒ ሙባረክን አወዳደቅ ያጤኗል !

ባላፈው ሳምንት የዩናይትድ ስቴትስ ውጭ ጉዳይ መስሪያ ቤት ከፍተኛ ባላሥልጣን የሆኑት፤ ማዳም ዊንዲ ሽርማን፤ የተበሉ ወይዘሮ፤ አዲስ አበባ ተገኝተው፤ የወያኔን አስከፊ ሥርዓት፤ ቅበዐ-ቅዱስ ለመቀባት መሞከራቸውን የኢትዮጵያ ሕዝብ በአርምሞ አዳምጦ ታዝቧቸዋል። ዛሬ፤ ሀገሪቱ፤ በዴሞክራሲ መንገድ እንደምትመራ፤ ምርጫው ዴማክራሲያዊ እንደሚሆን፤ ሰብዓዊ መብቶች እንደተከበሩ፤ ፍትህ-ርትዕ እንደሰፈነና፤ ኢኮኖሚው እንደዳበረ ወዘተ ወዘተ ተናግረው፤ ያልጠየቋቸውን ዘበራርቀው ወደ ሀገራቸው ተመልሰዋል። የሚገርመው ግን፤ ሴትዮዋን ወደ ሀገራቸው ይዟቸው የበረረው አይሮፕላን ገና ዋሽንግቶን አይሮፕላን ማረፊያ ሳይደርስ፤ የወይኔ ነፍሰ ገዳይ ቡድን፤ ሀዘኑን ለመግለጽ የወጣውን የአዲስ አበባ ሀዘንተኛ ሕዝብ፤ በጭካኔ እየደበደበና እያቆሰለ መበታተኑ ነው ። ፍየል፤ ገመነዋን፤ ጭራዋ ሊሽፍንላት እንዳልቻለ ሁሉ፤ ወያኔም ፤ የአሜሪካዊቷን ባለሥልጣን ቅጥ ያጣ ግድፈት ሊደብቅላቸው አልቻለም ። ወይም " በዓላ ትፈለጥ " ( የራሷ ጉዳይ ነው ) ብሏቸዋል ማለት ነው ።

ግራም ነፈሰ ቅኝ ፤ ኢትዮጵያ ሀገራችን ዛሬ ወዳጅ-ዘመድ አጥታለች ። እጇም ፤ አመድ-አፋሽ ሆኖ ቀርቷል ። ወርቅ ያበደረችው ሁሉ፤ አፈር አልብሷታል። ወንድሞቻችን የደቡብ አፍሪካ ጥቁሮች ፤ በመከራቸው ወቅት ቆማ ፤ የድርሻዋን አበርክታ ነበር። ዛሬ፤ በደቡብ አፍሪካ ተሰድደው የሚኖሩት ወገኖቻችን በግፍ ተረሽነዋል ። በዱላ ተቀጥቅጠዋል ። በዕሳት ተቃጥለዋል ።

የነብዩ ሞሐመድ ቤተ ሰቦች ተሰድደው ወደ ኢትዮጵያ ሲመጡ፤ ሀገራችን በክብርና በሀዘኔታ ተቀብላ አስተናግዳቸዋለች። ሃይማኖታችውንም በነፃነት እንዲያመልኩ ሠላምንና ፍቅርን ሰጥታቸዋለች። በፈቃዳቸውም ጊዜ ወደ ሀገራቸው እንዲመለሱ ተባብራለች። ይህም ታሪካዊ ተግባር፤ ኤል ሓዲስ በተሰኘው የነብዩ ሞሐመድን ዝክረ- ነገር በመዘገበው መጻህፍ ሰፍሮ እንደሚገኝ፤ ኢትዮጵያውያን እስላሞች አባቶች ዘወትር ያስታውሱታል።

በአንድ አምላክ የሚያመልኩ ኢትዮጵያውያን ምዕመናን ሁሉ፤ እስላሞችም ሆኑ፤ ክርስቲያኖችም በአንድ ላይ፤ የመጽሀፍ ሕዝቦች ይባላሉ ። ሁሉም በሠላምና በፍቅር አብረው እንዲኖሩ ሃይማኖታችው ያዝዛቸዋል። ኢትዮጵያውያን ምዕመናንም፤ ይህንን ትእዛዝ አክበርው በሠላም ኖረዋል ። ወደ ፊትም አብረው በሠላም ይቆያሉ።

ባለፈው ሣምንት፤ በሊቢያ በረሃ የተገደሉት ወገኖቻችንን፤ በሃይማኖት ስም የገደሏቸው ጽንፈኞችና አክራሪዎች ናቸው። አሸባሪዎች ናቸው ። ድርጊታቸው፤ የእስላም ሃይማኖትን ትዕዛዛትንና ህግጋትን የሚጻረር ነው። ለዚህ ነው በመላው ዓለም የሚኖሩ የሁሉም ሃይማኖቶች ተከታዮች በኅብረት ወንጀሉን ያወገዙት። በኢትዮጵያም ፤ ሙክራቦች፤ ቤተ ክርስቲያናትና መስጊዶች በመተባበር ለሟቾቹ የኅሊና ፀሎት አድርሰዋል ። አዝነዋል ። ግድያውንም ኮንነዋል ። አውግዘዋል።

የሀገራችን መከራ የሚወገድበት ጊዜ ሩቅ አይሆንም ። በመላው ዓለም የሚፈስሰው የኢትጵያውያን ደም ከመጉረፍ የሚቆምበት ጊዜ ሩቅ አይደለም። የሰማዕታቱም ቀን የሚከበርበትና የሚዘከርበት ቀን ይመጣል። ሀገራችን፤ የነፃነት ፀሀይ የሚፈነጥቅባት ሀገር ሆና ትነሳለች። የኢትዮጵያ ጠላቶች አንገታቸውን የሚደፉበት ወቅት ይመጣል ። ይህ ሁሉ ዕውን የሚሆነው ግን መሥዋዕትን የሚጠይቅ ቆራጥ ትግል በማካሄድ ብቻ ነው ። ያን ጊዜ ፤ የሚንቁን ይፈሩናል። ያከብሩናል። የሚጠሉን እንዲወድዱን ይገደዳሉ ። በክፉ ዓይን የሚያዩን ሁሉ ይቀርቡናል። ምን ጊዜም ቢሆን ሀገራችንን የማይወዱት ግን ሊወዷት አይችሉም። ወደዷትም ጠሏትም፤ ኢትዮጵያ ሀገራችን ግን በነፃነት መኖሯን ትቅጥላለች !

በዚህም ተባለ በዚያ፤ ሀገራችንን ከዘረኞች ጥፋት የምናድናት እኛው ራሳችን እንጅ፤ ሌላ ማንም እንደሌለ አምነን፤ ኢትዮጵያን ለማዳን እንነሳ! ሁሉም ተባብሮ ከተነሳ፤ ኢሕአፓ፤ ዛሬም እንድትላንቱ ፤ በግምባር - ቀደም ለመሰዋት ዝግጁ ነው !!

ኢትዮጵያ ለዘለዓለም ትኑር !